

# ጌዴዎን

- የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ከወጡ በኋላ በምድረ ከነዓን መኖር ጀምረዋል። ከተወሰኑ አመታት በኋላም በዚያ ምድር የሚኖሩ ከነዓናውያን የሚያመልኳቸውን ጣኦታት ማምለክ ጀመሩ። በዚህ ምክንያትም እግዚአብሔር ምድያማውያንን ተጠቅሞ ቀጣቸው። እግዚአብሔርም መልአኩን ጌዴዎን ተብሎ ወደሚጠራው ሰው ላከ። መልአኩም ጌዴዎንን "እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው እጅ እንድታድናቸው መርጦሃል።" ብሎ ነገረው። ጌዴዎንም በሰማው ነገር እርግጠኛ ስላልነበር ይህ ነገር ከእግዚአብሔር እንደሆነ ማረጋገጥ ፈልጎ ምልክትን ወይንም ተአምራትን ጠየቀ።

- ጌዴዎን ከ32000 ሰዎች ጋር ነበር ለውጊያ ዝግጅት ማድረግ የጀመረው። ሆኖም እግዚአብሔር የፈራ ካለ ወደቤቱ እንዲመለስ እንዲያደርግ ጌዴዎንን አዘዘው። ስለዚህም የፈሩት ወደቤታቸው ሲመለሱ 22,000 ብቻ ቀሩ! አሁንም የተመለመለው ሠራዊት ብዛት ስለነበረው እግዚአብሔር እንዲቀነስ ፈለገ። ስለዚህም ሌላ የመቀነሻ መንገድ እግዚአብሔር አዘጋጀ። እርሱም ውኃ እንዲጠጡ ማድረግ ነበር። ከፊሎቹ በጉልበታቸው ተንበርክከው ጎንበስ ብለው ከወንዙ ውኃ ይጠጡ ነበር። እንደዚህ ውኃ ሲጠጡ የነበሩትን ጌዴዎን አሰናበታቸው። ስለዚህም ወደቤታቸው ሄዱ። የቀሩት ግን ውኃ በእጃቸው ከወንዙ እያነሱ ልክ ውሻ ውኃ እንደሚጠጣ እነርሱም እንደዚህ አድረገው ጠጡ። እነኝህ ለጦርነቱ ተመረጡ። ቁጥራቸውም 300 ነበር። ምንኛ ትንሽ ሠራዊት ነበር! እግዚአብሔር ይህን ያደረገው እስራኤላውያን በራሳቸው ብርታት ድል እንዳደረጉ እንዳያስቡ ነበር።

- ከዚህ በኋላም ጌዴዎንና ከእርሱ ጋር የነበረው ትንሽ ሠራዊት በሸለቆው ውስጥ መሽጎ የነበረውን የምድያማውያንን ሠራዊት ከበበ። ከጌዴዎን ጋር የነበረው እያንዳንዱ ሰው በቀኝ እጁ ቀንደ መለከትና በግራ እጁ ደግሞ በማሰሮ ውስጥ የሚበራ ችቦ ይዞ ነበር። ጌዴዎን ምልክት ሲሰጣቸውም እያንዳንዱ ሰው ቀንደ መለከቱን ነፋ፤ ችቦውንም አበራ። ከዚያም "የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ" ብለው ጮኹ።

✵ ምድያማውያን በብዙ ሰራዊት የተከበቡ እስኪመስላቸው ድረስ ግራ ተጋቡ። እርስ በርሳቸውም ተጨራረሱ። ጌዴዎንም 300 ሰዎች ባሉት ሠራዊት ከምድያማውያን ጋር ተዋግቶ ድል አደረገ።

*ይህ የጌዴዎን ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በመሳፍንት መፅሐፍ ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 8 ድረስ ነው።*

http://gardenofpraise.com